# « ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም »

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

መንደርደሪያ

አንቺ ዶሮ ! ማነው ባልሽ ?!

አውራ ዶሮ !

ምን ያበላሻል ?!

ተበድሮ !

ምኑን ይከፍላል?!

መሬት ጭሮ !

መሬት ሲጭር፤

እዛው ፍንችር !!

ውይ ! ውይ ! ውይ ! እያሉ የሚጫወቱት ለቅሶ መሰል የልጆች ጨወታ ታወሰኝ ::

እንዳሁኑ ሳይሆን ዱሮ፤ ያኔ ጥንት፤ ባገር ወግ፤ ባገር ባህልና ቋንቋ፤ ልጆች ሲጫወቱ : ለዛ ነበረው « ለዚያም ነበር እረኛ ምን ብሎ ዘፈነ ?» ይባል የነበረው ::
የሕዝብ ብሶት፤ ያስተዳደር በደል፤ ብሎም ትንቢት ቢጤም፤ በልጆች አንደበት ይነገር ነበርና ለልጅ አግዜር ያሳየዋል ! ይባላል ::

መግቢያ

የኢትዮጵያ ፓርላማ ለ2003 ዓ.ም. በጀት የ77.2 ቢልዮን ብር:

- በ 360 ድጋፍ
- ያለምንም ተቃውሞ
- በ26 ድምጽ ተዐቅቦ አጽድቋል::

ከዚሁ ውስጥ፤ 20 ቢልዮን ብር : ከውጪ በሚመጣ ብድርና እርዳታ የሚሸፈን ሲሆን :

የደሞዝ ጭማሪም እንደሚኖር : ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል ::

የሰሞኑ የጀሮ ብራና ጠላቸ ዜና ! አስገራሚው የ360ቹ ደጋፊዎች ጉዳይ ነው፤ ዘወትር በአንድ ቀለበት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ድግም ድግግሞች !!

በአንድ ጽሑፌ ላይ እንዳቀረብኩት፤ አቶ መለስ ዜናዊ የአማርኛ ቋንቋን የሚገለገሉበት፤ ኢትዮጵያዊያንን ለመስደቢያ፤ ለመዝለፊያና ለማዋረጃ መሆኑን ገልጬ ነበር፤ አሁንም የሆነው ይኸው ነው ::

የ2003 ዓ.ም. በጀት ውሳኔን ተመርኩዞ ፤

« ብድርና እርዳታው ቢቀር ከየት መጥቶ በጀቱ ይሸፈናል ? » ተብሎ ለቀረበው የአቶ ልደቱ አያሌው ጥያቄ የሰጡት መልስ፤

« መሃይም : በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ መሃይም :: አላዋቂ : በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ አላዋቂ :: አክራሪ ኒዮ ሌበራሎችንና : ፈረንጅን መለየት ያልቻለ » ብለው በማበሻቀጥ ነበር መልስ የሰጡት :: ተቀባዩ እንደ ምርቃት ካልቆጠረው በስተቀር ::
(በቀይ ቀለም የሰፈረው : አቶ መለስ ዜናዊ : በፓርላማ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ ነው )

እዚህ ላይ የምንረዳው፤ ወያኔ ግልጋሎታቸውን የጨረሱ ታማኝ ተቃዋሚዎችን፤ እንደሚጣል የወሲብ መፈጸሚያ ላስቲክ፤ እንደ ጥንቱ አባባል እንደ አሮጌ ቁና፤ ወዲያውኑ አሽቀንጥሮ መጣል የለመደ መሆኑን ሲሆን ቀጣዩ የማን ተራ ይሆን ? ብለን እንድንጠይቅ ይጋብዘናል ::

አቶ ልደቱ ካልቆነጠጡት የማይገባው ሆኖ እንጂ : የአቶ መለስ አባባል : « ፈረንጆችን፤ እኛ የምናውቃቸውን ያህል፤ አንተ አታውቃቸውም » ነው መልክቱ ::

ጂሚ ካርተር « እነመለስን እናውቃቸዋለን፤ ከጫካ ጀምረን ኮትኩተን፤ እዚህ ያደረስናቸው እኛ ነን » ማለቱን : አቶ ልደቱ የሆዱ ሞራ፤ ጆሮውንና አይምሮውን ደፍኖት፤ ባለማጤኑ ይኸው ለዛሬው ሆድ ቀትር ስድብ ተዳረገ ::

« እሰይ ! የዘላለሚን አገኘሁ ! » እንዳለው ሌባ ሆነብኝና ገረመኝ ::
እናንተዬ ?! ይኸ የድሃ አምላክ ለፍርድ አለመቸኮሉ እንጂ : ለካስ እሩቅ አይደለም ጃል?!

ዕድሜውን ይስጠን፤ ገና ብዙ እናያለን !

አንድ የአገር መሪ : (መሪ ከተባለና ከሆነ) ማለቴ ነው : እመራዋለሁ ለሚለው ሕዝብና አገር: ከበሬታ፤ ፍቅር፤ ይቅርባይነት፤ እጅግ መጣም የበዛ ትዕግስትና አስተዋይነት : ይጠበቅበታል :: ዜጎች ቢሳሳቱም የማስተማርና : የመምከር ሃላፊነቱን በመገንዘብ : የሚገባቸውን ክብር በመስጠት: በምላሹ ክብር ይቸረዋል :: በአንጻሩ : ከአቶ መለስ የምናየውና የምንሰማው : ዜጎችን መናቅ፤ ማቅለል፤ መስደብና ማሽማቀቅ፤ በመሆኑ በሚመሩት ሕዝብ ዘንድ : በምሳሌነት ከመጠቀስና ከመከበር ይልቅ : ከጥጥ የቀለሉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ::

*አንድ ሰው ፡ ግብዝ ካልሆነ በስተቀር ፡ ምንም ተማርኩ ቢል፡ ሁሉን አውቃለሁ ማለት አይችልም ። እያንዳንዳችን በተማርነው ሞያ ጠቀም ያለ ዕውቀት ሲኖረን፤ ከሞያችን ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ደግሞ፡ መጠነኛ ወይም ውሱን ግንዛቤዎች ሊኖሩን ይችላሉ ፡ ያ ደግሞ ፍጹም ከስህተት ውጪ ነው ማለት አይደለም ። አንድ ሰው ሁሉን ማወቅ አለበት፡ የሚባልበት የአልባማክ (encyclopedia) ዘመን ካከተመ ቆይቷል ።*
*ጠቅላላ ዕውቀትን በተመለከተ፤ እንደ አስተዳደጋችን፤ የቤተሰብ አቅም፤ የምንኖርበት ዘመን፤ ያለንበት አካባቢ ሕብረተሰብ ዕድገትና ስልጣኔ፤ የዕውቅት መሳሪያዎች አቅርቦት፤ የማንበብና የማወቅ ፍላጎታችን፤ ለምን ? እንዴት ? መቼ ? በምን ምክንያት ? የት ? ማን ? ከማን ጋር? ...ወዘተ ብለን በምናነሳቸው ጥያቄዎችና መምናገኛቸው መልሶች ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ያም ሆኖ ከሞላጎደል ስህተት አይጠፋውም ።*

*ለሰው ልጅ አስከፊው ነገር፡ መሳሳቱ ሳይሆን፤ ከነስህተቱ መሞት ነው፡ በበለጠ የሚጎዳው ።* (il ne faut pas mourir idiot) *ይላሉ ፈረንሳዮች « ደደብ እንደሆንክ አትሙት » ማለት ነው በኛ ቋንቋ መሳ ለመሳ ሲለወጥ ።*
*አቶ ልደቱ ያቀረበው ጥያቄ፡ ነውርነት ወይም ስህተት ኖሮት ሳይሆን፤ ኮንትራቱን ለጨረሰ ታማኝ ተቃዋሚ፤ ለመሰነባበቻ የቀረበ ው፡ የኮመጠጠ ጠላ ግብዣ መሆኑ እንጂ !!*

*ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ፡ የበጀት ቁጥጥር አድርጎ የማያውቅ፤ በንቅዘትና በሥልጣን ብልግና የተዘፈቀው፤ የወያኔ መንግሥት፤ በአንድ ትውልድ ብቻ ሳይሆን፤ በሁለትና በሦስት ትውልድ ፡ ተከፍሎ በማያልቅ ብድር ፡ አገራችንን ዘፍቆ፤ ዜጎችን በብድር ውቅያኖስ ውስጥ ካሰጠመ በኋላ፤ « ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም » ብሎ የቀፈፈውን የብር አራጣ ፡ በልመና አቁማዳው ሸክፎ ፡ እብስ ! ለማለት እንዲያመቸው፤ የሂሳብ ነገር ሲነሳ ፡ ቁስሉ ላይ ጨው የነሰነሱበት ያህል ይቆጠቁጠዋል ።*

*እናም ፡*

*ምን ያበላሻል ?!*

*ተበድሮ !*

*ምኑን ይከፍላል?!*

*መሬት ጭሮ !*

*መሬት ሲጭር፤*

*እዛው ፍንችር !!* *ሆኖ ፡ እንስቅ ወይ እናለቅስ ይሆን ?!*

*በቸር ይግጠመን !*

*ሰኔ 26/ 2002 ዓ.ም. (July 3/ 2010)*